## የ MKVን አገልግሎት የሚያገኙት

### ባሉበት ትምህርት ቤት መቆየት
የተንከባካቢዎቹ ፍላጎት ከሆነ እና ተማሪው(ዋ)ን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ

### ወዳሉበት ትምህርት ቤት መጓጓዣ ማግኘት
በወላጅ ወየም በተንከባካቢ ሰው ጥያቄ።

### ነፃ የትምህርት ቤት ምግብ ማግኘት
የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ማግኘት

### ወዲያውኑ ትምህርት ቤት መመዝገብ/መግባት
ምንም እንኳ በተለምዶ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ባይኖሩም ወዲያውኑ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይደረጋል። እነዚህ አስፈላጊ ሰነዶች ት/ቤት ከተመዘገቡና ከገቡ በኋላ ሊሰበሰቡ ይችላሉ

### የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ተደራሽነት
የመስክ ጉዞ እገዳን ማንሳት፣ በስፖርት እና በክለቦች መሳተፍ፣ ከትምህርት በፊት/በኋላ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ

### የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች
ትንንሽ ልጆችን ለጨቅላ ልጆች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር በማገናኘት ያግዙ

ሌላም፣ ሌላም...

## ከፈለጉ፣ እባክዎን ከዚህ በታች የሚመለከታቸውን አካላት ያግኙ።

- የትምህርት ቤት ደህንነት ቡድን
- የተማሪዎች ፐርሶኔል ሰራተኛ (PPW)
- የት/ቤት ካውንስለር

**አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት፡-**
**MKVSERVICES@MCPSMD.ORG**
**240-740-4511 ኢሜል ያድርጉ/ይደውሉ።**

MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

DEPARTMENT OF EDUCATION · UNITED STATES OF AMERICA

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*



# የማኪኒ–ቬንቶ አገልግሎቶች
# MCKINNEY-VENTO SERVICES

## ትምህርት ለሁሉም:
## ምንም መሰናክል አይኖርም፣ መማር ብቻ

# MKV አገልግሎት ለማግኘት ብቃት የሚኖረው ማነው?

ቋሚ፣ መደበኛ፣ እና በቂ ማደሪያና መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች።

## ለ MKV እርዳታ አመላካች ሁኔታዎች

- የመጓጓዣ አውቶብስ አለማግኘት
- ረሃብ
- ከት/ቤት ማርፈድ፣ መዘግየት፣ ወይም መቅረት።
- የንጽህና ችግር
- በድካም ምክንያት ክፍል ውስጥ መተኛት፣ ማንቀላፋት
- ተሳትፎ አለማድረግ/ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እጥረት
- አስፈላጊ አጠቃላይ ህክምና የጥርስ ህክምና ጨምሮ ይላገኙ።
- ወደ ተለያዩ ትምህርት ቤቶች መግባት፣ ሪከርድ አለመኖር፣ የትምህርት መቋረጥ
- ማህበራዊ እና የባህሪ ተግዳሮቶች



## ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ በአንዱ የሚኖር/የምትኖር ሰው ያውቃሉ?

### መጠለያ/መሸጋገሪያ ቤት

ይህ በቤት ውስጥ ግጭት ምክንያት ወደ መጠለያ መግባት፣ ቤት የሌላቸው የሚቆዩበት መጠለያ፣ የወጣቶች መጠለያ፣ በፌደራል የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኤጀንሲ የሚሰጡ ተጎታች ቤቶች፣ ፈጣን የመልሶ ማቋቋም በመሳሰሉት ፕሮግራሞች የተከፈለባቸው መኖሪያ ቤቶች፣ የመሸጋገሪያ መኖሪያ ቤቶች፣ ወዘተ. ያካትታል።

### ሆቴል/ሞቴል

o የተለየ አማራጭ ባለመኖሩ በሞቴል/በሆቴል ውስጥ መቆየት።

### ከሌሎች ሰዎች ጋር ተዳብሎ መቆየት

መኖሪያ ቤት በመወሰዱ ምክንያት፣ በኢኮኖሚ ችግር፣ ወይም በተመሳሳይ ምክንያት ከሌሎች ጋር ተዳብሎ መኖርን ያካትታል።

### መጠለያ የሌለው

ይህ መኪና ውስጥ መኖር፣ በመናፈሻ ቦታዎች፣ በሕዝብ መናኸሪያ ቦታዎች፣ ወና በሆኑ ሕንፃዎች፣ ደረጃ ያልጠበቁ መኖሪያ ቤቶች፣ አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያዎች፣ ወይም ተመሳሳይ ቦታዎች ላይ መቆየትን ይጨምራል።